በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ 206729
ህዳር 28 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው
ተሾመ ሽፈራው
ሀብታሙ እርቅይሁን
ብርሃኑ መንግስቱ
ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡ ኦቶሪኖ ከአንገት በላይ ሕክምና ማዕከል ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ጠበቃ ፍክርተ ጥበቡ -ቀረቡ

ተጠሪ፡ ነርስ ሚካኤል ዳንኤል- ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የስራ ዉል መቋረጥ አግባብነት የሚመለከት ነዉ፡፡ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን የአሁኑ አመልካች ላይ ባቀረበው ክስ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ከሐምሌ 16 ቀን 2010ዓ.ም ጀምሮ በፕሮፌሽናል ነርስ የስራ መደብ በወር ብር 11,200 ደመወዝ እየሰራሁ እያለ የዲስፕሊን ጥፋት ፈጽመሃል በማለት በ08/01/2013 ዓ.ም በህገ ወጥ መንገድ ከስራ አሰናበተኝ በማለት ስንብቱ ህገወጥ ነዉ ተብሎ የህገወጥ ስንብት ክፍያዎች እንዲከፈለው ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን አመልካች በበኩሉ ባቀረበው መልስ ተጠሪ በቀን 08/01/2013ዓ.ም በነበረው ስብሰባ ላይ ሁከትና አምባጓሮ በመፍጠርና ለድብድብ በመጋበዝ በስራ ቦታ ረብሻና ሁከት በማድረጉ በአዋጅ ቁ/1156/2011 አንቀጽ 27(1)ረ መሰረት ያለማስጠንቀቂያ የሚያሰናብት የስነምግባር ጉድለት መፈጸሙን፣በኦፕራሲዮን ክፍል ውስጥ ዋና ሀኪም የሚናገረውን ንግግር በሹፈት በመድገም የታካሚ ስነልቦና እንዲታወክ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ያደረገ በመሆኑ ባህሪውን እንዲያስተካክል በቅርብ አለቃው በቀን 30/07/2020 የቃል ማስጠንቀቂያ የተሰጠው ቢሆንም ነሐሴ 19 ቀን 2012 ዓ.ም ንግግሩን በመድገም የታካሚ ስነልቦና የሚጎዳ ንግግር በመናገሩ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶ በፈፀመዉ ጥፋት ያለማስጠንቀቂያ የተሰናበተ መሆኑን፣የዓመት እረፍት እና ያልተከፈለ ደመወዝ እንዲወስድ ቢጠየቅም ፈቃደኛ ስላልሆነ የሚከፈል ክፍያ ባለመኖሩ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በማለት መከራከሩን መዝገቡ ያሣያል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኝ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ በወቅቱ ስብሰባ ላይ የነበሩ ሰዎች ምንም ፀብና አምባጓሮ እንዳልነበረ እና ተጠሪ በስራ አካባቢ ያለው ግንኙነትም መልካም መሆኑን የገለጹ ስለሆነ በድርጅቱ ባለቤቶች በግነት የተገለጸዉ ማስረጃዉ ተጠሪን የማይገልጽ መሆኑን ችሎቱ አምኗል፣ስለዚህ ተጠሪን ለማሰናበት የሚያስችል ጥፋት ያልፈመ እና ፀብ እና አምባጓሮ እንዲሁም የታካሚን ስነልቦና መጉዳት የተባለው በማስረጃ የተረጋገጠ ባለመሆኑ የተጠሪ ስንብት ህገወጥ ነው በማለት የተጠየቃቸዉ ልዩ ልዩ ክፍያዎችን አመልካች እንዲከፈል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም የግራ ቀኝ ክርክር መርምሮ የአመልካች ምስክሮች ቃል በዘፈቀደ ውድቅ ተደርጓል የተባለው የመከላከያ ምስክሮች ቃል ተመዝኖ ውድቅ የተደረገ በመሆኑ በዘፈቀደ ውድቅ ተደርጓል ሊባል አይቻልም፣በቀን 08/01/2013ዓ.ም በስራ ቦታ /በቢሮ/ ውስጥ ፀብ እና አምባጓሮ ፈጥሯል የተባለው በእለቱ ከቢሮ እስከወጡ ድረስ የተፈጠረ ፀብ አለመኖሩ በግራ ቀኝ ምስክሮች ተረጋግጧል፣ስለዚህ በቢሮ ውስጥ የተፈጸመ ፀብና አምባጓሮ ሳይኖር ለጥያቄ ምላሽ ባለመስጠቱ ወይም ዝም በማለቱ ብቻ ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውል መቋረጡ ስንብቱን ህገወጥ የሚያደርግ ነው በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል እንዲታረም ሲሆን አቤቱታዉ ይዘት ባጭሩ ሲታይ፣ ተጠሪ በማኔጅመንት አባላት ስብሰባ ላይ እንዲገኝ የተደረገው ከድርጅቱ ሰራተኛ ጋር ያለውን የግል ጠብ አስወግደው የቡድን ስራውን በብቃት እንዲወጣ ለማስቻል ሲሆን ተጠሪ በስርዓት መልስ መስጠት ሲገባው እየጮኸና እጁን እያወናጨፈ በመደጋገም ስትፈልግ አባረኝ እያለ ለጠብ አጫሪነት የሚጋብዝ ሐይለ ቃል የተሞላበት የንቀት ንግግር መናገሩ ቀጥሎም ዋና ዳይሬክተሩን ለመደብደብ መጋበዙና የፋይናንስ ኃላፊው ላይ መዛቱ በአዋጁ አንቀጽ 27(1(ረ)) መሰረት የስራ ውልን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችል በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ይህ አምባጓሮ ሊሆን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አይችልም፣ሞራል የሚነካ ንግግር ሊሆን አይችልም፣ከዚህ በፊት በኮሊደር ላይ ለጠብ የሚጋብዝና መዛት አምባጓሮ ፈጽሟል የተባለው በቃል የስራ ውሉን አቋርጣችሁ በኋላ ወደ ስራ መልሳችሁ እንደገና በዚህ ምክንያት የስራ ውሉን ሊታቋርጡ አትችሉም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ተጠሪ በስራ ቦታ ፀብና አምባጓሮ መፍጠሩን፣ለድብድብ መጋበዙን እና ዶ/ር ላይ በማሾፍ የቡድን ሥራውን የበደለ እና የታካሚ ሥነ ልቦና የጎዳ ንግግር መናገሩን ባጠቃላይ ድርጊቱ የአዋጁን አንቀጽ 27(1(ረ)) ስር የተመለከተውን ጥፋት የሚያሟላ መሆኑ ከፍተኛ የማኔጅመንት አባላት የምስክርነት ቃል ሳይተችና ሳይመዘን ሙሉ በሙሉ ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡በተጨማሪም በስብሰባ ላይ የተገኙ የማኔጅመንት አባላት የዲሲፕሊን ጥፋት ስለመፈፀሙ በስብሰባ ቃለ-ጉባኤ ላይ የፈረሙትን ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ተሽሮ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልን በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረባቸውን የሰውና የሰነድ ማሰረጃዎችን ውድቅ በማድረግ ተጠሪ በሥራ ቦታ አምባጓሮ እና ፀብ አጫሪነት ተግባር መፈፀሙን መመስከሩን ከተቀበለ በኋላ ውድቅ በማድረግ ስንብቱ ህገወጥ ነው ያለበትን ከአዋጁ አንቀጽ 27/1/ረ/ አንፃር ለማጣራት ጉዳዩ ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ታዟል፡፡

ተጠሪ በቀን 15/10/2013ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ ተጠሪ የዲሲፕሊን ጥፋት ፈፀመ የተባለው በቀን 08/01/2013 ዓ.ም ሲሆን በማኔጅመንት ስብሰባ ወይም ለስራ በተደረገ ስብሰባ ላይ ሳይሆን ሲ/ር አሰፋ ሙሉነህ እና አቶ አብዱላዚዝ መሐመድ የተባሉ ሰራተኞችን ለማስታረቅ በተደረገ ስብሰባ ላይ ተጠሪም ከአቶ አብዱላዚዝ ጋር አይነጋገሩም እርሱም ይጠራና እናስታርቃቸው ተብሎ ከተጠራሁ በኋላ ወ/ሮ ቲማጅ እኔንም ዘግቶኛል ብለው ሲናገሩ ካንቺ ጋር ደግሞ ምን ያገናኝናል ብሎ ተጠሪ በሚጠይቅበት ወቅት ዶ/ር ኢሳቅ በድሪ አለቃህ ናት በስነ ስርዓት አናግራት ሲለው ተጠሪ ምላሽ ሳይሰጥ ዝም ያለ ሲሆን እንዳውም ከስራ አባርራሃለው ሲለው ተጠሪ ከፈለክ አባርረኝ በማለቱ እንደጥፋት ተቆጥሮ ወዲያውኑ በቃል ከስራ በማሰናበት በጥበቃ ከግቢ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡ተጠሪ በሌላ ቀን ለክፍያ ጥያቄ በሄደበት ወቅት በትዕቢትና በንቀት አለቆችን በማነጋገርና በመሳደብ፣ለጥል በመጋበዝና በመዛት የሚል የስንብት ደብዳቤ ተሰጥቶኛል፡፡የቀረቡት የአመልካች ምስክሮች ጭምር እና ገለልተኛ ምስክሮች ተጠሪ በቢሮ ውስጥም ሆነ ከቢሮ ውጭ የፈፀመው ፀብና አምባጓሮ እንደሌለ አረጋግጧል፡፡ስለዚህ የስር ፍ/ቤት ተጠሪ የዲሲፕሊን ጥፋት መፈፀሙ አልተረጋገጠም በማለት

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ስንብቱ ህገ ወጥ ነዉ በማለት የሰጠዉ ውሳኔ የህግ ስህተት የለውም፡፡የሰነድ ማስረጃን በተመለከተ አመልካች ያቀረበዉ ቃለ ጉባኤ ተጠሪ በቃል ከስራ ከተሰበተ በኋላ እና በምን ምክንያት ውይይት እንደተደረገ፣ በምን ላይ እንደተስማሙ የማይገልፅ እንዲሁም የተሰበሰቡትም የዲሲፕሊን ኮሚቴ ሳይሆን ዶ/ር ይስሀቅ የሰበሰባቸዉ ሰዎች በስብሰባ ላይ የተገኙ የሚል እንጂ ድርጊቱ ስለመፈፀሙ ምስክር ወይም ውሳኔ ሰጪ ነን በማለት የፈረሙት አይደለም፣ስለዚህ ፍ/ቤቱ ይህንን አመዛዝኖ ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ነው፤የስር ፍ/ቤት የሰውና የሰነድ ማስረጃ መርምሮ ተጠሪ ፀብና አምባጓሮ ስለመፈፀሙ አመልካች ያላስረዳ መሆኑን በማረጋገጥ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበት የህግ ምክንያት ባለመኖሩ አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክሯል፡፡አመልካች አቤቱታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥ አንጻር የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘበነዉ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረዉ አሰሪና ሰራተኛ የስራ ዉል የተቋረጠዉ በአመልካች አነሳሽነት መሆኑ አልተካደም፡፡ለዚህም በምክንያትነት የተገለጸዉ ተጠሪ በስራ ቦታ ጸብና አምጓሮ በመፈጸም ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘቱ ስንብቱ ህጋዊ ነዉ የሚል መከራከሪያ አቅርቧል፡፡የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27/1/ረ ላይ እንደተደነገገዉ እንደጥፋቱ ክብደት በስራ ቦታ ላይ በአምባጓሮ ወይም ጠብ አጫሪነት ተጠያቂ መሆኑ የተረጋገጠ ሰራተኛ የስራ ዉሉ በአሰሪዉ አነሳሽነት ሊቋረጥ ይችላል፡፡

አመልካች የተጠሪን የሥራ ዉል ያቋረጠዉ ተጠሪ በስራ ላይ በፈጸመዉ ጥፋት ነዉ በማለት የተከራከረ በመሆኑ ይህንኑ የማስረዳት ሸክም የአመልካች ስለመሆኑ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 258-259 እና የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2001 ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባል፡፡በተያዘዉ ጉዳይ ለስንብቱ ምክንያት ነዉ የተባለዉ ተጠሪ በስራ ቦታ አምጓሮና ጠብ ፈጥሯል፤እንዲሁም የታካሚ ስነልቦና የሚጎዳ ንግግር በማድረግ ጥፋት ፈጽሟል የሚል ሲሆን ይህንኑ በማጣራት ረገድ ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን ስልጣን ያላቸዉ የስር ፍርድ ቤቶች በግራ ቀኙ በኩል የቀረበዉን ማስረጃ አመዛዝነዉ ተጠሪ የተባለዉን ድርጊት ስለመፈጸሙ አልተረጋገጠም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡አመልካች አሁንም አጥብቆ የሚከራከረዉ የስር ፍርድ ቤቶች የማስረጃ ምዘና ስህተት ፈጽመዋል በማለት ነዉ፡፡በሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘዉ ጭብጥም የምስክሮች ቃል

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ድርጊቱ ስለመፈጸሙ አስረድተዉ እያለ ዉድቅ መደረጉን አግባብነት ለመመርመር የሚል ነዉ፡፡

በመሰረቱ የሰበር ችሎቱ ስልጣንና ሃላፊነት የመጨረሻ ዉሳኔ በተሰጠባቸዉ ጉዳዮች ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞ ሲገኝ ይህንኑ የማረም እንጂ ፍሬነገር የማጣራት፣ማስረጃ የመመርመር እና የመመዘን ጉዳይ የሚመለከት አለመሆኑን ከሰበር ስርዓት መሰረታዊ ዓላማ የምንገነዘበዉ ጉዳይ ነዉ፡፡የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ ይዘትና መንፈስ ይህንኑ የሚያመለክት ሲሆን ህገ መንግስቱን ተከትሎ የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 የሰበር ስልጣን መሰረታዊ የህግ ስህተት ማረም የሚመለከት እንደሆነ በጥቅሉ የሚደነግግ ሲሆን ይህንኑ እና ማሻሻያ አዋጆች የሻረዉ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 በሰበር ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሚያሰኙት ሁኔታዎች ምንድናቸዉ ለሚለዉ ትርጉም ሰጥቷል፡፡የአዋጁን አንቀጽ 2/4/ እና 10 ይመለከቷል፡፡አዋጁ በዚህ መልኩ መቀረጹ በዋናነት ሰበር ሰሚ ችሎት የተቋቋመበትን ዓላማ፣ አንድ ወጥ የህግ አተረጓጎም እንዲኖር እና የዉሳኔዎችን ተገማችነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ስራዎችና ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸዉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በመስጠት እንዲሰራ የተዘረጋ ስርዓት መሆኑን ነዉ፡፡ስለዚህም ሰበር ችሎቱ ማስረጃ የመመርመር ስልጣን የሌለዉ መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡

በሌላ በኩል ሰበር ችሎቱ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ የመመርመር ስልጣን የለዉም ሲባል የስር ፍርድ ቤቶች በክርክር አመራር ረገድ፣በማስረጃ አቀባበል እና ምዘና የሚመለከቱ መሰረታዊ መርሆዎች አተገባበር ጋር በተያያዘ የፈጸሙትን ስህተት የማረም ሃላፊነትን የሚያስቀር ሊሆን እንደማይገባ እንገነዘባለን፡፡በፍርዱ ላይ የማስረጃ አቀባበልና ምዘና ስህተት ተፈጽሟል ለማለት የሚቻለዉ በተከራካሪ ወገኖች የተቆጠረ ማስረጃ ያለበቂ ምክንያት ሳይሰማ ሲታለፍ፣በማስረጃ አቀባበል ረገድ የተከራካሪ ወገኖች እኩል የመደመጥ መብት አለማከበር፣የማስረዳት ሸክም የማነዉ የሚለዉን አለመለየት ወይም የማስረጃ ተገቢነት፣ተቀባይነትና ምዘና ረገድ አግባብነት ያለዉን መርህ ባለመከተል እንዲሁም በመሰረታዊ ህግ ወይም በስነስርዓት እና የማስረጃ ደንብ ቅቡልነት ያላቸዉን የማስረጃ ህግ መርሆዎችን ባለመጠበቅ የሚሰጡ ዉሳኔዎችን የሚያጠቃልል ስለመሆኑ ይህ ሰበር ችሎት ከዚህ ቀደም በተለያዩ መዝገቦች ላይ ከሰጠዉ ፍርድ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡በዚህ ረገድ በሰበር መ/ቁ/37105፣29861፣47551፣49660 እና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ የሰጠዉን ዉሳኔ መመልከት ይቻላል፡፡

የአመልካች አቤቱታ ከዚህ አኳያ ሲታይ በተለይም የድርጅቱ ባለአክስዮን የሆኑት ባልና ሚስት የሰጡት የምስክርነት ቃል ይዘት ግንት ይታይበታል መባሉ የፍርድ ቤቱን የማስረጃ ምዘና

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ስህተት ያሚያል በማለት ያቀረበዉን ቅሬታ አጽንኦት በመስጠት መርምረናል፡፡ ከማስረጃ ምዘና ጋር በተያያዘ አንዱ መሰረታዊ መርህ የማስረጃዉ የማስረዳት ብቃት ወይም ክብደት የመመርመር ጉዳይ ነዉ፡፡አንድን አከራካሪ ፍሬነገር መኖር/አለመኖሩ ወይም መፈጸም/አለመፈጸሙ የሚረጋገጠዉ የቀረበዉን ማስረጃ ይዘትና ክብደት/weight of evidence/ በማመዛዘን ስለመሆኑ የማስረጃ ደንብ የምያስገነዝበን ጉዳይ ነዉ፡፡የአንድ የማስረጃ ክብደት ከሚመዘንባቸዉ ሁኔታዎች አንዱ የማስረጃ ሰጪዉ አካል ወይም የምስክሩ ገለልተኝነት እና ተአማንነት ወይም የማሳመን አቅሙን መመርመር ይጠይቃል፡፡የገለልተኝነት መርህ የሚያወሳዉ ማስረጃ ሰጪዉ ወገን በአከራካሪዉ ጉዳይ ወይም ዉጤቱ ላይ ያለዉ ፍላጎት ወይም ጥቅም መኖር/አለመኖር ጋር ተገናዝቦ መመዘን ያለበት ስለመሆኑ ነዉ፡፡የማስረጃ ተአማንነትም የሚመዘነዉ ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር ያለዉ አንድነት እና ልዩነት እንዲሁም ከተፈጸመዉ ሁኔታ ወይም ድርጊት ጋር ተነጻጽሮ ነዉ፡፡ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለዉ ለማስረጃዉ የሚሰጠዉ ክብደት የሚወሰነዉ ከእነዚህ መመዘኛዎች ድምር ዉጤት አንጻር ነዉ፡፡በመጨረሻም በፍትሓብሔር ጉዳይ አከራካሪዉ ፍሬነገር መኖር/አለመኖሩ ወይም መፈጸም/አለመፈጸሙን በሚመለከት ከድምዳሜ የሚደረሰዉ ከተከራካሪዎቹ ጉዳዩን በተሻለ ደረጃ ``preponderance of evidence``በማስረጃ የትኛዉ ወገን አስረድቷል የሚለዉን መርምሮና አመዛዝኖ መሆን አለበት፡፡በዚህም ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ በስራ ቦታ አምባጓሮ እና ጠብ ፈጽሟል ወይ? የሚለዉ ጭብጥ ላይ የግራ ቀኙን ማስረጃ በመመርመር ሂደት አመልካች ካቀረባቸዉ ምስክሮች ዉስጥ ሁለቱ የድርጅቱ ባለአክስዮን የሆኑት ባልና ሚስት መሆናቸዉን እና ምስከሮቹ የሰጡት ቃል ከሌሎች ምስክሮች ቃል ጋር በማነጻጸር ሲመዘን ግነት ይታይበታል ብሎ ከመግለጽ ዉጪ ማስረጃዉ አግባብነት /relevancey/ ወይም /inadmissibille/ ተቀባይነት የለዉም የሚል አቋም አልወሰደም፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ ፍርድ ቤቱ ማስረጃ ሲመዝን የምስክሮቹ ቃል ግነት ይታይበታል ማለቱ ብቻዉን የማስረጃ ምዘና መርህ ጥሰት ፈጽሟል የሚያሰኝ አይደለም፡፡

ሌላዉ የአመልካች የቅሬታ ነጥብ በአመልካች በኩል የቀረበዉ ቃለ ጉባዔ ዋጋ አልተሰጠዉም የሚል ሲሆን ከዉሳኔዉ እንደተገነዘብነዉ ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን ስልጣን ያለዉ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ሰነዱን መርምሮ ሰነዱ የተዘጋጀበት ሁኔታ አስተዳደራዊ ዉሳኔ የተሰጠበት የሚመስል እንጂ የዲስፕሊን ክስ ቀርቦ ተጠሪ ባለበት ተሰምቶና ተጣርቶ ዉሳኔ የተሰጠበት አለመሆኑን ፍርድ ቤቱ ያረጋገጠዉ ፍሬነገር ጉዳይ ነዉ፡ይህ ከሆነ ደግሞ ማስረጃዉ ዋጋ አልተሰጠዉም ወይም አልተመረመረም የሚባል ዓይነት አይደለም፡፡ከዚህ ሁሉ

መገንዘብ የሚቻለዉ በማስረጃ አቀባበልም ሆነ ምዘና ረገድ በስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ ስህተት አለመኖሩን ነዉ፡፡

ሲጠቃለል ተጠሪን ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ለማሰናበት የሚያስችል ጥፋት መፈጸም አለመፈጸሙን ከማረጋገጥ አኳያ የግራ ቀኙን ማስረጃ በመመርመርና በማመዛዘን ለስንብት የሚያበቃ ጥፋት መፈጸሙ አልተረጋገጠም በማለት የስራ ዉሉ የተቋረጠዉ ከህግ ዉጪ ነዉ በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የደረሰቡት ድምዳሜ ላይ በማስረጃዉ አቀባበል እና ምዘና ረገድ ቅቡልነት ያላቸዉን መርሆዎች ተከትሎ የተወሰነ ነዉ ከሚባል በስተቀር በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/ 2013 አንቀጽ 2/4/ እና 10 ድንጋጌ መሰረት ለሰበር ችሎቱ ከተሰጠዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የማረም ስልጣን አንጻር በዉሳኔዉ ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚባልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ዉሳኔ

1ኛ/በዚህ ጉዳይ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/165191 በቀን 26/04/2013ዓ.ም የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ችሎት በመ/ቁ/ 258122 ላይ በቀን 13/08/2013ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ ጸንቷል፡፡

2ኛ/በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

3ኛ/በዚህ መዝገብ ላይ በቀን 23/09/2013ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረዉ የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ

**መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡**

ማ/አ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም